# ትግላችን ከማን ጋር?

ይህንን አርእስት የመረጥኩበትን ምክንያቶ በተቻለ መጠን ከብዙው በጥቂቱ ለመዳሰስ እሞክራለሁ። በመሰረቱ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በድርጅት ስር ተሰባስቦም ሆነ በተናጠል ፣ አሁን ያለውን የትግሬ ወያኔዎችን አገዛዝ እታገላለሁ ብሎ ሲነሳ፣ ለምንና እንዴት እንደሚታገላቸው ጥርት ያለ አቋምና ፣ ለድልም የሚያበቃው መሰረታዊ የሆኑ፣ ካብዛኛው የተቃዋሚ ቡድን፣ ወይም ሕብረተሰብ፣ ጋር አብሮ ለመስራት የሚያስችለው ቅድመ ዝግጅቶች ሊኖሩት ይገባል። በመጀመሪያ ወያኔ ጸረ ሕዝብና ጸረ ኢትዮጵያ የሆነ ድርጅት ስለሆነ መወገድ አለበት በሚለው አቋም ላይ ሁሉም የጋራ የሆነ አንድ አይነት ስምምነት ላይ መድረስ መቻል አለባቸው። በአንጻሩም ሌሎች ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑ ድርጅቶች ላይም ያላቸውን ግንዛቤና አቋም ግልጽ ባለ ሁኔታ ማቅረብ መቻል አለባቸው። እነዚህ ከወያኔ ውጪ ጸረ ኢትዮጵያ አቋም ያላቸው ድርጅቶች (OLF,ONLS,SNLF,AFD) በቀደሚነት የሚጠቀሱ ይሆናሉ። ይህንን በቅጡ ማሟላት ከተቻለ ብቻ ነው መልክ ያለውና አላማው የጠራና የተስተካከለ፣ ብሎም የሰከነ ትግል ለማካሄድ የሚቻለው ። ይህ ሊሆን ባለመቻሉ ግን አሁን ያለንበት ወይንም የደረስንበት ምስቅልቅል የሆነ ማ ማንን እየታገለ እንደሆነ ለመናገር የሚያዳግትበት ሁኔታ ላይ ለመድረስ የበቃነው። ስለሆነም አሁን ወያኔ እግሮቹን ዘርግቶ፣ እጆቹን አጣምሮ፣ እኛ ማለትም ወያኔን እየታገልን ነው እያልን በራሳችን በምናሾፈውና በምንቀልደው እርስ በእርስ እየተዘነጣጠልን በምናሳየው ትርኢት የወያኔ መሳቂያና መሳለቂያ፣ የወገንና የሐገር ማፈሪያ ከመሆናችን ባሻገር፣ ከውጪ ሆኖ ለሚመለከተንም የምዕርቡ ዓለም ወያኔ ከኛ የተሻለ እንደሆነ በምናሳየው ምስቅልቅልና ቅጥ የለሽ ጫጫታን ከመደገፍና ከማስተናገድ ገሸሽ እንዲሉና ለወያኔ እምነትንና ከፍተኛ ድጋፍ እንዲሰጡ በማድረግ አውቀንም ይሁን ባለማወቅ ከፍተኛ ሚና እየተጫወትን ነው።

ከምርጫ 97 ሽንፈት በኋላ የትግሬ ወያኔ በቅንጅትና በሌሎችም ተቃዋሚ ድርጅቶች ላይ ባደረሰው ግድያ፣ ጭፍጨፋና እስራት የተነሳ በሐገር ቤት ያለውን ትግል ለጊዜውም ቢሆን ለዘብ ያድረገው ቢመስልም በአንፃሩ ግን በምዕራቡ ዓለም የሚገኘው የተቃዋሚው ፓርቲ ደጋፊዎች ሊቆጣጠር ባለመቻሉ የተነሳ ትግሉ በ (Diaspora) ከምን ጊዜውም በላይ እንዲፋፋም እረድቷል ስለሆነም (Diaspora)ው ለትግሬው ወያኔ ውጋት ሆነውበት እንደቆዩ ለሁላችንም የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ይህ በምዕራቡ ዓለም የተቀጣጠለው ምድር አንቀጥቅጥ ትግል እንዳጀማመሩ ሊቀጥል አልቻለም፣ ይህም የሆንበት ዋነኛው ምክንያት የ (AFD እና KIL) በመባል የሚታወቁት ሁለት ድርጅቶች ምስረታና የአመሰራረታቸው ተንኮል የተሞላበት አካሄድ እንደሆነ በተለያዩ ጽሑፎችም ሆነ ቃል መጠይቆች በሰፊው ተተችቶበታል፣ የነዚህ ሁለት ድርጅቶች ምስረታ ነበር ትግሉ ሃዲዱን ስቶ ብሎም እንዲኮታኮት ትልቅ አስተዋጽዖ የተጫወቱት ቢባል አባባሉ ከእውነት የራቀ አይሆንም። ይህ ሁኔታ እንዲፈጠር ታላቅ ሚና የተጫወቱትና በዋነኝነት ሊጠቀሱ የሚችሉት የስልጣን ጥመኞች ስብስብ የሆነው ቀስተደመና በመባል የሚታወቀው በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የሚመራው ድኩማንና የሱ ጋሻ ጃግሬዎች ለፈስፋሳና ተንበርካኪነት አቋም እንደሆነ ለማንም ያልተሰወረ ሃቅ ነው። ለትግሉ መሽመድመድ የቀስተደመና ቡድን አጃቢና ጋሻ ጃግሬዎች የተጠቀሙበት የአደረጃጀትና የብተና ስልት (KIL) በሚለው በዋነኛነት ሲመራ በአንፃሩ በሌላው ወገን የተሰለፈው ማለትም በነ ሻለቃ

ዮሴፍ የሚመራው ደግሞ (AFD) በመባል የሚታወቀውን ጸረ ኢትዮጵያ አቋም አራማጅ የሆነውን ቡድን በመፍጠርና ለማጠናከርና የሚያደርጉት ደፋ ቀና ትግሉ እንዲሽመደመድ አሌ የማይባል አስተዋጽዖ አበርክቷል። እዚህ ላይ የ (KIL) አቀንቃኞችም (AFD) ተቀባይነት እንዲያገኝ በማራገቡ ላይ ካማናቸውም ያልተናነሰ ወይም የበለጠ ሚና ተጫውተዋል። ይህ በዚህ ሁኔታ ለሁለት ዓመታት ሲታመስ ነበር ሕብረተሰቡ ዋናውና ሊታገለው የሚገባውን የትግሬን ወያኔን ተወት በማድረግ እርስ በእርሱ መናቆር የጀመረው። ይሄም ስር እየሰደደ መጥቶ ባለበት ሁኔታ ነበር የአምባ ገነኑ የወያኔ አገዛዝ ወደ እስር ተወርውረው የነበሩትን የተቃዋሚው ቡድን (ቅንጅት) መሪዎችን ከእስር የፈታውና የተፈቱትም የተቃዋሚው ቡድን መሪ ተብዬዎች ለሁለት ዓመት እየነደደ በነበረው የ(Diaspora) ትግል ላይ ቤንዚን በማርከፍከፍ ወደከፋ ሁኔታ እንዲሸጋገር ያበቁት። እነዚሁ የተቃዋሚው ፓርቲ መሪዎች ወደ (Diaspora) መምጣት ትግሉ ከድጡ ወደማጡ እንዲወርድ አድርጎታል፣ ዋናው የትግሉ አውድማ ሐገር ቤት መሆኑ ቀርቶ ትግሉ ወደ (Diaspora) ስለተሸጋገረ (Diaspora) ላይ ተጠቅቻለሁ እኔን ለመምታት ወይንም እኔን ለማውረድ የቀስተዳመና ሰዎች በፈጠሩት (KIL) ጉዳት ደርሶብኛል ያለው በኢንጂነሩ የሚመራው ቡድን (KIC) የሚባል ሌላ ውዥንብር ፈጣሪ የሆነ አካል በመመስረቱ በአመራሩም በኩል ግልጽ የሆነ አለመግባባትና ልዩነት እንዳለ ይፋ ሆነ። ይሄም ሁኔታ መፍትሄ ሳያገኝ በመቅረቱ ልዩነቱ እየሰፋ መጥቶ አንዱ አንዱን መወንጀሉና ጣትን መቀሰሩ ከተከታዩ ሕብረተሰብ አልፎ መሪ ተብዬዎቹም ጎራ ገብቶ ሲያምሳቸው ቆይቶ በሽታው ከ(Diaspora) አልፎ ሐገር ቤት በወ/ሮ ብርቱካን ተሽካሚነት በመዛመቱ ሐገር ቤት ያለውም ሕበረተሰብ ምስቅልቅሉ እየወጣ እንደሆነ በየ እለቱ የምነሰማውና የምናነበው የዘመናችን ታላቁ ድራማ ሆኗል።

ይሂ የመበታተንና የመመሰቃቀል ሁኔታ በቅንጅት አካባቢ ብቻ አልቀረም፣ ትርምሱ በሕብረቱም ዘንድ እንደወረርሽኝ በሽታ ተዛምቶ በተለይ በአንጋፋነቱና በፖለቲካ ጥራቱ ቀዳሚነት የያዘው ብሎም ወያኔን በመታገል ባለው አቋሙና በቁርጠኛንነቱ የሚነገርለት ኢሕአፓ ውስጥ ዘልቆ በመግባት የረጅም ዘመን የትግልና የአቋም ጥራት ያለውን ኢሕአፓንም እያተራመሰው ይገኛል። በአቋሙ ጥራት የሚታወቀው ይኸው ቡድን ለሁለት ተከፍሎ አንዱ በአቋሙ ሲጸና ተገንጥሎ የወጣው ቡድን ለሰላሳና ከዚያም በላይ በሆነውና የማይናወጠው አቋሙ ተለውጦ 180° በመዞር የወያኔው ቱባ የሰዬ አብርሃ የትግል አጋር በመሆን “ ወጣ ወጣና እንደሸንበቆ ተንከባለለ እንደ ሙቀጫ” የሚል ስያሜ አሰጥቷቸዋል። ለነገሩ የዚሁ አሁን የኢሕአፓ አንጃ በመባል የሚታወቀው ቡድን ያበቃለት (current affaires discussion forum) በመባል የሚታወቀው የወያኔ ስውር አጀንዳ አራማጅ የሆነ ክፍል ውስጥ እንዲመጡና መርዛቸውን እንዲተፉ ከተደረጉ በኋላ ነበር መርዛቸውንም ተፍተው ከ(Cobra)ነት ወደ ( garden snake)ነት የተሸጋገሩት ይሄው ዛሬ ለማዳ እባብ ከሆኑ ውለው አድረዋል። እንግዲህ ይህ ሁሉ ምስቅልቅል በመሃከላችን እያለ እራሳቸውን ቅንጅት እያሉ የሚጠሩት ቡድኖች ሆኖም ግን እርስ በርስ የሚዘናጠሉት ከሶስትና ከአራት ቡድን ተከፍለው ባለበት፣ ሕብረት ውስጥም ካሉት በአንጋፋነቱ የሚጠቀሰው ኢሕአፓ ከሁለት ተሰንጥቆ የእርስ በእርሱ ውንጀላው በተፋፍመበት በአሁኑ ጊዜ እውን ጠላታችንን ለይተን አውቀናል ለማለት ይቸግራል፣ ለምንና ማንን እንደምንታገል የምናውቅም አይመስልም ። በአሁኑ ወቅት ወያኔን ከምንታገለው የበለጠ እርስ በእርሳችን አንዱ አንዱን ለማንኳሰስና ለመጣል የምናባክነው ግዜ ሰዓትና ጉልበት በአብዛኛው ያመዝናል ቢባል ከእውነት

የራቀ አይሆንም። ተቃዋሚ ነኝ ባዩ ሁሉም በየፊናው ወደራሱ የሕዝብን ድጋፍ ለማሰባሰብ የሚያደርገው ትግል ላይ ነው እንጂ ያተኮረው ወያኔን እየታገለ እንዳልሆነ ለማንም ሚስጢር ሊሆን አይችልም። ወያኔን እየታገልን ነው ካልንም እራሳችንን እያታለልን ነው ማለት ነው። ሁላችንም ወያኔን እየታገልን ነው እንላለን በአንፃሩ ግን የጋራ ጠላታችን ወያኔ ከሆነና የምንታገለውም ይህንኑ የወያኔን አገዛዝ ገርስሶ ለመጣል ከሆነ ፣ እንደምንለውም እኛ ሕዝባዊ የሆነ አቋም አለን ብለን ካመንን ሌላኛውም ቡድን ጸረ ወያኔ አቋም አለው ሆኖም ግን አንዳንድ አነስተኛ የሆኑ እነሱ የሚያራምዱትን አቋም አልስማማበትም ከተባለ ለጊዜው ይህንን አነስተኛ አለመግባባት ወደጎን አድርጎ በአንድ ላይ ሊያራምደን የሚችለውን አቋም በማራመድ በሕብረት ይህንን ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ ሕዝብ የሆነን የትግሬ ወያኔን ለመታገል የሚያስችለን አንድነት ለመፍጠር እንዴት ተሳነን? ሊያስተባብረንና አንድ ሊያደርገን የሚችሉ ነጥቦች ላይ ከማተኮር ይልቅ ሊለያዩንና ሊበታትኑን በሚችሉ ጉዳዮች ላይ በከፍተኛ በማተኮራችን እርስ በእርስ በምናደርገው አተካራ ለወያኔ ካለን የትግል ጽናት ይልቅ አንዳችን አንዳችንን ለመጣል ያለን ጽናት፣ ጊዜና ጉልበት ጎልቶ በመውጣቱ አንዲት ስንዝር እንኳ ለመራመድ አልቻልንም። ይህ ልዩነታችን በድሕረ ገጽ አዘጋጆች፣ በሬድዮ ፕሮግራም አዘጋጆችና በየ (Paltalk) በሰፊው ሲንጸባረቅ ይታያል። አንድ አቋም አለን የሚሉት የ(Paltalk) ክፍሎች እንኳን በአንድ ተሰባስበው በአንድነት መታገል ሳይችሉ በአንፃሩ የፖለቲካ ቡድኖችን ሲተቹ ሳይ በጣም ይደንቀኛል፣ ሌሎችን ከመተቸታቸው በፊት ለምን እነሱ በአንድ ክፍል ተሰባስበው እራሳቸውን አንድ አድርገው ከዚያ የፖለቲካ ቡድኖች ወደ እንድነት እንዲመጡ ለማድረግ አይሞክሩም? ችግሩ ሁላችንም የራሳችን ወደል ስህተት ሳይታየን በሌላው ላይ ያለው ቅንጣት ስህተት ጎልቶ ይታየናል ይህ አይነት አመለካከት በጠቅላላ በድርጅት የታቀፈውም ሆነ በግለሰብ ደረጃ የሚንጸባረቅ እራስን ፍጹም አድርጎ የመመልከት አባዜ በሁላችንም ኢትዮጵያውያን ላይ ሳናውቀው በላያችን ላይ ጎጂውን የሰራ አጉል አመለካከት እንደሆነ ብንረዳው ዛሬ ከደረስንበት አሳዛኝና አስፋሪ ሁኔታ ባልደረስን ነበር።

ከላይ በመነሻዬ ላይ እንደጠቀስኩት ማንን እንደምንታገልና ለምን እንደምንታገል ስንታገልስ የትግላችን መርሆ ሊሆን የሚገባውን ዋና ዋና ነጥቦች በማያሻማ ሁኔታ ማስቀመጥ ካልቻልን፣ እንታገላለን ወይንም እናታግላለን ማለቱ ቀቢጸ ተስፋ ከመሆን አያልፍም። ትግላችንም አላማውን ሳይስት ከግቡ እንዲደርስ ለማድረግ የትግል አጋራችን ልናደርጋቸው የምንችላቸው ቡድኖች ልናራምደው የሚገባ መሰረታዊ የማታገያ ጽንሰ ሃሳቦች ሲኖሩንና ጠላትና ወዳጅ ብሎም እንደ ዋነኛ ጠላት የምንፈርጃቸውንና የማንፈርጃቸውን ለይተን ማወቅ ስንችል ነው። ከጠላትነት እንደ ወይኔ ልንፈርጃቸው ባንችልም ሆኖም ግን በኢትዮጵያ ሕልውና ላይ አደጋ ሊያደርሱ ወይንም የወደፊት እንቅፋቶች ሊሆኑ ይችላሉ ብለን የምንመድባቸውን ቡድኖች ጋራ ሊኖረን የሚገባው ግንኙነትና ልናስተምራቸው የሚገባ መሰረታዊ ነጥቦችን በማንሳት የነሱን ተከታዮች የትግላችን አጋር ልናደርግ የምንችልበት ኢትዮጵያዊ አጀንዳን ስንነድፍና የትግል መርሆ ሲኖረን ነው ። ይህ ከሞላ ጎደል ሲሳካ ብቻ ነው የወያኔን አገዛዝ ከስር ከመሰረቱ ገርስሠን ጥለን ኢትዮጵያዊነት የተላበሰ በትግል ተፈትኖ በትግል የተወለደ ሕዝባዊ ስርአት በሐገራችን ልናመጣ የምንችለው እንጂ ይህ ሁኔታ ባለተሟላበት ሁኔታ ታግለን የትግሬ ወያኔን እንጥላለን ማለት አሁን ባለንና በያዝነው የትግል ዘይቤ ወያኔ ከነኑ ባሰለፋቸው ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑ ምዕራባውያን ሐገሮችና በታሪካዊ የኢትዮጵያ

ጠላትነታቸው የምንውቃቸውን የአረብ መንግስታት ከአጠገቡ አሰልፎ ባለበት በአሁኑ ወቅት ልናመጣ የምንችለው ውጤቱ  ውሃ ከመውቅውጥ አይልፍም፣ ስለሆነም ሁላችንም ልቦና ስጥቶን ወደ ህሊናችን ተመልሰን ቁርሾንና ማን ከኔ በላይ የሚለውን መመጻደቅ ከህሊናችን ፍቀን አውጥተን ለውድ ሐገራችንና ለተተኪው ትውልድ ማፈሪያ ሳንሆን መኩሪያ የሚሆነንን እውነተኛ ተግባር መተግበር ስንችል ብቻ ነው። ይህንን ማሟላት ሳንችል ታግለን ሕዝቡን ለድል እናበቃዋለን ማለት እራስን ካለማወቅ ብሎም የጠላትን አቅምና ብርታት ካለመገንዘብ የፈለቀ ደካማ አመለካከት ካልሆነ በቀር ሌላ ትርጓሜ ሊሰጠው አይችልም።

ከሰውነት ዳኜ

ሰሜን አሜሪካ

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!